Montgomery County Public Schools

### የወላጅ/የሞግዚት መመሪያ

# የግላዊ የትምህርት ፕሮግራም ዝግጅት/ግምገማ ቡድን ስብሰባ-Individualized Education Program (IEP) Development/Review Team Meeting

ተማሪው(ዋ) ለልዩ ትምህርት ብቁ መሆኑ(ኗ) ከተረጋገጠ በኋላ፣ የሚቀጥለው እርምጃ የተማሪው(ዋ)ን IEP ማዘጋጀት ይሆናል። IEP ማለት የተማሪው(ዋ)ን ፍላጎት የሚያሟላ ግላዊ የአገልግሎቶች እቅድ እና ፕሮግራም ነው። ተማሪው(ዋ) የሚያሳየውን/የምታሳየውን ለውጥ ለመለካት የት/ቤት ሠራተኞች የሚጠቀሙበትን ዓመታዊ ግቦችን እና ዓላማዎችን ፣ እንዲሁም ተማሪው(ዋ) የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዲፕሎማ ወይም የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሠርተፊኬት ፕሮግራም ለማጠናቀቅ እየተከታተል(ች) እንደሆነ ዝርዝር ነገሮችን ያካትታል። የመጀመሪያ የግምገማ ስብሰባ በተደረገ 30 ቀናት ውስጥ የመጀመሪያ IEP መዘጋጀት አለበት። ከወላጅ/ከሞግዚት ስምምነት/ፈቃድ እስከሚገኝ ድረስ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን አይሰጥም። በሜሪላንድ ውስጥ፣ ስምምነት/ፈቃድ የሚያስፈልገው ለመጀመሪያው IEP ብቻ ነው። የመጀመሪያ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመስጠት ከወላጅ የጽሑፍ ፈቃድ/ስምምነት በተጨማሪ፣ ጁላይ 1/2017 ተግባር ላይ በዋለው የሴኔት ድንጋጌ/Senate Bill 710፣ የተሻሻለው "Section 8–405, Education Article of the Annotated Code of Maryland" መሠረት፣ የሚከተሉት ተጨማሪ መስፈርቶች በወላጅ ስምምነት ውስጥ ይካተታሉ፡-

የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም ቡድን የሚከተሉትን ካቀረበ/ከጠየቀ ከወላጅ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡-

1. ልጅን ለሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ክሬዲት በማይሰጡ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ማስገባት (የአማራጭ ትምህርት ማዕቀፍ/ከሪኩለም ወይም አማራጭ የትምህርት ውጤት)
2. ልጅን ከስቴት አማራጭ የሥርዓተ ትምህርት/ከሪኩለም ጋር ለሚጣጣም ተለዋጭ/አማራጭ ትምህርት ግምገማ ለይቶ ማወቅ፣ ወይም
3. የልጁን/የልጅቱን ባህርይ ለመቆጣጠር ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም በሚዘጋጅበት ጊዜ ማቀቢያ/መግቻ ወይም ገለልተኛ ማድረግን ማካተት ያስፈልጋል።

እነዚህ ሃሳቦች የቀረቡት በእያንዳንዱ ተማሪ በግል ሁኔታዎች/ፍላጎቶች ላይ ተመሥርቶ ስለሆነ ለእያንዳንዱ/ለማንኛዉም ተማሪ ተስማሚ ላይሆን ይችላል። የተማሪው(ዋ)ን IEP ለመገምገም እና ተማሪው(ዋ) ዓመታዊ ግብ ላይ ለመድረስ መሻሻል/ለውጥ እያሳየ(ች) እንደሆነ ለመወሰን የ IEP ቡድን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ስብሰባ ማድረግ ይጠበቅበታል። በዚህ ወቅት፣ ስለ IEP ማናቸውም ክለሳ ማድረግ አስፈላጊ የሚሆን ከሆነ ቡድኑ ይነጋገራል። የ IEP ቡድን በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ስብሰባ እንዲያደረግ የሚጠበቅበት ቢሆንም፣ ወላጅ/ሞግዚት ወይም የት/ቤት ቡድን የ IEP ቡድን ስብሰባ እንዲደረግ በማናቸውም ጊዜ ለመጠየቅ ይችላሉ።

## የ IEP ቡድን ጥንቅር፡-

- ወላጆች/ሞግዚቶች።
- የእርስዎ ልጅ የአጠቃላይ ትምህርት (General education) መምህር/ት፣ ልጅዎ በመደበኛው የትምህርት አካባቢ ዉስጥ በመሳተፍ ላይ ወይም ምናልባት ይሳተፍ/ትሳተፍ እንደሆነ።
  - » የእርስዎ ልጅ የአጠቃላይ ትምህርት (general education) አስተማሪ ከሌለው/ከሌላት፣ ወይም የትምህርት ቤት እድሜ ያልደረሰ(ች) ከሆነ፣ የአጠቃላይ ትምህርት (general education) መምህር በእርስዎ ልጅ ዕድሜ ያሉትን የማስተማር ብቃት ያለው/ያላት ባለሙያ ግለሰብ ይሆናል/ትሆናለች።
- የልዩ ትምህርት መምህር/ት።
- የ IEP ቡድን ስብሰባ ሊቀመንበር የሆነዉ/ችዉ...
  - » ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች የሚፈልጉት ልዩ የትምህርት አይነትን ለማሟላት በተለየ ሁኔታ የተዘጋጀ ትምህርት ለመስጠት ወይም ለመቆጣጠር የሙያ ብቃት ያለው/ያላት፣ እና
  - » ስለ ካሪኩለም እና በ MCPS ስለሚገኙ መገልገያዎች/resources እውቀት ያለው/ያላት።
- የግምገማው ውጤት የሚያስከትለውን የማስተማር አንድምታ መተርጎም የሚችል/የምትችል ግለሰብ።
- እንደአግባቡ፣ የተዛማጅ አገልግሎት ሠራተኞችን ጨምሮ፣ በእርስዎ ፍላጎት ወይም በትምህርት ቤቱ ምርጫ ስለ እርስዎ ልጅ እውቀት ወይም ልዩ የሙያ ችሎታ ያላቸው ሌሎች ግለሰቦች።
- አግባብነት ካለው፣ የእርስዎ ልጅ።

## እያንዳንዱ IEP ቡድን በተጨማሪ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

- የእርስዎ ልጅ ቀደም ሲል በ MCITP አገልግሎት አግኝቶ/ታ ከሆነ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጨቅላ ህፃናት እና ታዳጊ ልጆች ፕሮግራም/Montgomery County Infants and Toddlers Program (MCITP) ተወካይ።
- የመጀመሪያው IEP ሥራ ላይ እንደዋለ ሳይዘገይ ተማሪው(ዋ) 14 ዓመት ዕድሜ ሲሞላው(ት)፣ በእርስዎ ፈቃድ/ስምምነት የማናቸውም ተሳታፊ ኤጀንሲ ተወካይ ስለ (ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ግቦች እና ክዋኔዎች) የሽግግር ዕቅድ/transition planning ለመወያየት።
- እርስዎ ከጠየቁ፣ ለእርስዎ አስተርጓሚ።

ይቀጥላል

# ስለ ግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) የዝግጅት/ምልከታ ቡድን ስብሰባ የወላጅ/የሞግዚት መመሪያ

## ደረጃ 1

### ትውውቅ እና የስብሰባው ዓላማ(ዓላማዎች)፡-

- የ IEP ቡድን ተሳታፊዎች ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ። የስብሰባው ዓላማ ስለ እርስዎ ልጅ IEP ዝግጅት/ምልከታ መሆኑን ሰብሳቢው(ዋ)/ሊቀመንበሩ(ሯ) መግለጫ ይሰጣል/ትሰጣለች።

## ደረጃ 2

### ስለ IEP ዝግጅት፡-

- ቀጠሮ ከተያዘለት የ IEP ቡድን ስብሰባ ቢያንስ አምስት የሥራ ቀናት በፊት፣ አስገዳጅ ሁኔታዎች ካልተፈጠሩ በስተቀር፣ ማናቸውንም የግምገማ ግኝት ውጤቶችን፣ ሪፖርት፣ ዳታ/መረጃ፣ ቻርት፣ ወይም የIEP ቡድን በስብሰባ ላይ የሚወያይባቸውን ሌሎች ሠነዶችን ቅጂ ማግኘት አለብዎት።
- IEP የሚዘጋጀው ወይም ክለሳ/ግምገማ የሚደረገው ደረጃ-በደረጃ ሂደት ነው። የእርስዎ ልጅ ጥንካሬ እና የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ እና ለመርዳት/ለማገዝ የሚያስችሉ ቁሳቁሶች፣ መጠነኛ ለውጥ/መሻሻል ያለባቸው ነገሮች፣ እና ለእርስዎ ልጅ የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችን በሚመለከት ውይይት ይደረጋል። (ይመልከቱ IEP ምን ማካተት እንዳለበት  ስለ IEP ዝርዝር ነገሮች መረጃ/ኢንፎርሜሽን።)
- ስለ እርስዎ ልጅ ጠንካራ ጎኖች እና ትምህርታዊ ፍላጎቶች ለመወያየት ይዘጋጁ።

## ደረጃ 3

### የ IEP ቡድን ውሳኔዎች ማጠቃለያ/ቀደም ሲል የተጻፈ ማስታወሻ፡-

- ማንነት/መለያን ለመለወጥ ወይም ለመጀመር፣ ግምገማ፣ ወይም ስለ እርስዎ ልጅ የትምህርት ምደባ ወይም ለልጅዎ ተገቢውን ነፃ የፐብሊክ ትምህርት ስለመስጠት ከትምህርት ቤቱ ስለቀረበው ፕሮፖዛል ወይም ተቀባይነት አለማግኘት የሚገልጽ ማስታወሻ MCPS በጽሑፍ ይሰጣል።
- በ MCPS የ IEP ቡድን አባላት ተቀባይነት ያላገኙ ማናቸውም ከእርስዎ የቀረቡ ጥያቄዎች በዚህ ማጠቃለያ ላይ በሠነድነት ይያዛሉ።
- ለመልሶ ማቋቋሚያ/መርጃ አገልግሎቶች ተደራሽነት እንደሚከተለው በቃል እና በጽሑፍ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ይሰጥዎታል።
  - » በእርስዎ ልጅ የመጀመሪያ IEP ቡድን ስብሰባ።
  - » ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በእርስዎ ልጅ ዓመታዊ የግምገማ ስብሰባ።
  - » የእርስዎ ልጅ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆን/እንድትሆን ለማስቻል ተዛማጅነት ያለው ተጨማሪ አገልግሎት እንዲሰጥ ያቀረቡት ጥያቄ ከፀደቀ ወይም ተቀባይነት ካላገኘ።

## ደረጃ 4

### ክትትል፡-

- የተሞሉት የ IEP ሠነዶች በሚስጥራዊ የት/ቤት ፋይል ይቀመጣሉ። ከ IEP ቡድን ስብሰባ ቀደም ሲል የተጻፈ ማስታወሻን ጨምሮ፣ የተሞሉ የወረቀት ስራ ቅጂዎችን፣ IEP ስብሰባ በኋላ አምስት የሥራ ቀናት በፊት፣ የት/ቤት ሠራተኞች ቅጂዎችን ይሰጡዎታል።